# ጭምብልና ቆቡ

ቀድሞ የበቀለን ፣ ወፍ እንደሚፈጀው
ቀድሞ የተናገረን ፣ መቼም ሰው አይበጀው ፣
ይህንን አባባል ፣ ግምት አስገብቼ
ጊዜ እንስጠው ባዩን ፣ ለተስፈኛ ትቼ
እራሴን ለትችት ፣ ግንባሬን ሰጥቼ
ጆሮዬ የሰማውን ፣ ያዩትን አይኖቼ
እስኪ ልናገረው ፣ ምን ይሉኝን ትቼ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ በእጅጉ ስቷል
ያሳፈረው ባቡር ፣ ከሃዲዱ ወጥቷል
ይነካው ሳያጣ ፣ የሰው ቁስል ነክቷል
ወልቃይት ጠገዴን ፣ እጅግ አስቆጥቷል
ለህውሃት ብሎ ፣ የንብ ቀፎ ከፍቷል
ያቶ አብይ አቋም ፣ ማንነቱ ታይቷል
ከእንግዲህ ሰውየው ፣ እንደመለስ ሞቷል ።

ስንት ጀግና ሞቶ ፣ ስንቱ እንዳላለቀ
አይነኬን ነክቶ ፣ ትግሉን ካዋደቀ
የአማራ እይታው ፣ ፈሩን ከለቀቀ
አፉ እንደ ፊሻሌ ፣ እንዲህ ከባረቀ
ሌላም ይኖረዋል ፣ ድብቅ የታመቀ
አይበጅህም እሱ ፣ አለቀ ደቀቀ
እንኳንም በጠኋት ፣ ጭምብሉ ወለቀ ።

ከሰሜን ከደቡብ ፣ እንዲ እየከነፈ
አላስተውል ብሎ ፣ አፉ ካላረፈ
ገና ከጅምሩ ፣ ድንበሩን ካለፈ
መንገድና ውሃ ፣ ብሎ ከወረፈ
እወቀው ከማን ጎን ፣ እንደተሰለፈ
ከነ ሃጎስ ጉያ ፣ ገብቶ እንደታቀፈ
የባሰው ይመጣል ፣ ነገ እየገዘፈ
ጥቃቱ ይቀጥላል ፣ ከቃላት ባለፈ ።

ሰልችቶናል እኛ ፣ የወያኔ ፣ ኢቃ ኢቃ
ካርድ እየለወጡ ፣ እንዴት እንጠቃ
ጉልቻን መቀየር ፣ አይበጅንም ይብቃ
ከነግሳንግሱ ፣ ይውረድ ፣ ከሰው ጫንቃ
አዲሱ ሹመኛ ፣ አልጣመንም በቃ ።

ህዝብ እንዳልመረጠው ፣ እያወቀው ልቡ
ለጆሮ የሚጥም ፣ ታሪክ በማቅረቡ
እንይ ብሎ ነበር ፣ ህዝቡም በሃሳቡ
ግና ሳይጀመር ፣ ታለፈ ከገደቡ
እሰጋለታለሁ ፣ እንዲያውም በቅርቡ
እጁን ደም ሳይነክር ፣ አይቀርም ታዘቡ
ወልቆ እናየዋለን ፣ ጭምብልና ቆቡ ።

ታዛቢው

April 17, 2018